OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የYouth Arts (ወጣቶች ስነ-ጥበብ) 2026 መመሪያዎች

## የገንዘብ ድጎማ አጠቃላይ እይታ

የYouth Arts የገንዘብ ድጎማ በSeattle የሚገኙ የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለስነ-ጥበብ እና ለባህል ትምህርት እድሎች የተሻለ ተደራሽነት እንዲያገኙ የሚረዳ የ2 ዓመት ፕሮግራም ነው። እነዚህ ፕሮግራሞች የሚከናወኑት ከትምህርት ሰዓት ውጭ ሲሆን፣ ክህሎት ባላቸው አርቲስቶች እና በአስተማሪ አርቲስቶች ይመራሉ። ግቡ ከተለያዩ የዘር እና የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ዳራዎች የተውጣጡ ወጣቶች ከስነ-ጥበብ ጋር የሚገናኙባቸው ተጨማሪ እድሎችን መፍጠር ነው።

እንደ ማመልከት፣ ብቁነትዎን መፈተሽ ወይም ኦንላይን የገንዘብ ድጎማ ሥርዓቱን መጠቀም ካሉ ነገሮች ጋር በተያያዘ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም እገዛ ካስፈለገዎት ወደሚከተለው አድራሻ ኢ-ሜይል ይላኩ፦ YouthArts@seattle.gov።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪዲዮ በኩል) ጨምሮ በእርስዎ ቋንቋ ሊያነጋግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** እርስዎ ብቻ ይደውሉልን እና የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። ወደ ጥሪው የሚቀላቀል አስተርጓሚ እስከናገኝ ድረስ ለጥቂት ጊዜ መስመር ላይ መጠበቅ ሊኖርብዎት ይችላል። በተጨማሪም YouthArts@seattle.gov ላይ ኢ-ሜይል በመላክ ለስብሰባ ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።

## ማመልከቻ

በSeattle ከተማ አስተዳደር የገንዘብ ድጎማ ድር-ጣቢያ አማካኝነት ኦንላይን ያመልክቱ።

የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነት ከሌለዎት በተቻለ ፍጥነት ሠራተኞችን ያነጋግሩ።

## ማመልከቻ ማስገቢያ ቀነ ገደብ

**ማክሰኞ፣ ማርች 10 ቀን 2026 ዓ.ም፣ 5 ፒ.ኤም ፓሲፊክ ሰዓት።**

እባክዎ ማመልከቻዎን ለማጠናቀቅ በቂ ጊዜ ይስጡ። 5 ፒ.ኤም ፓሲፊክ ሰዓት ላይ ከተቀመጠው ቀነ ገደብ በኋላ የሚገቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

## ብቁነት

- ፕሮጀክቶች ከሴፕቴምበር 2026 ዓ.ም – ኦገስት 2027 ዓ.ም እንዲሁም ከሴፕቴምበር 2027 ዓ.ም – ኦገስት 2028 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ መከናወን ይኖርባቸዋል።
- ብቁ አመልካቾች በግለሰብ ደረጃ የሚሰሩ አርቲስቶች፣ አስተማሪ አርቲስቶች፣ የጥበብ እና የባህል ድርጅቶች፣ የወጣቶች አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች እና ዲግሪ የሚሰጡ ተቋማትን ያካትታሉ።
- ፕሮግራሞች በመካከለኛ እና/ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች ክፍት መሆን ያለባቸው ሲሆን፣ በSeattle ከተማ ወሰን ውስጥ መከናወንም ይኖርባቸዋል። ጥያቄዎች ካሉዎት የፕሮጀክት አስተዳዳሪውን ያነጋግሩ።
- አካላዊ መገኛ አድራሻዎ ከSeattle ከተማ ወሰን ውጭ ሊሆን ይችላል።

- በተሸላሚዎች የሚቀጠሩ ሁሉም አርቲስቶች እና አስተማሪ አርቲስቶች ፕሮጀክቱ ከሚመለከተው የእድሜ ክልል እና ከጥበብ እና/ወይም ከባህላዊ ዘርፎች ጋር በተያያዘ ቢያንስ የአንድ (1) ዓመት የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።
- ፕሮጀክቶች ከላይ **የገንዘብ ድጎማ አጠቃላይ እይታ** ውስጥ እንደተገለጸው የYouth Arts የገንዘብ ድጎማ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች እና የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት።

## የገንዘብ ድጋፍ

የተመረጡት ተሸላሚዎች በሁለት (2) ዓመታት ውስጥ በሚከናወኑ ፕሮግራሞች ዘንድ የሚከፋፈል በድምሩ **$12,000** የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ፡- በ2026-2027 $6,000 እና በ2027-2028 $6,000።

## የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች

ይህን የገንዘብ ድጎማ አስመልክቶ እና ምርጥ ማመልከቻ እንዴት ማቅረብ ይቻላል በሚለው ዙሪያ የበለጠ ይወቁ። የእርስዎን ፕሮጀክት ለሚመለከት ልዩ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ከመረጃ ክፍለ-ጊዜዎቹ አንዱን ይታደሙ።

### የጥያቄ እና መልስ ክፍለ-ጊዜ 1

**ሐሙስ፣ ፌብሩዋሪ 12፣ 2026 ዓ.ም፣ ከ12 – 1 ፒ.ኤም**
ለፌብሩዋሪ 12 ቦታ ይያዙ

### የጥያቄ እና መልስ ክፍለ-ጊዜ 2

**ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ 17፣ 2026 ዓ.ም ከ5 – 6 ፒ.ኤም**
ለፌብሩዋሪ 17 ቦታ ይያዙ

### የማመልከቻ ረቂቅ ግምገማ ክፍለ-ጊዜ 1

**ረቡዕ፣ ፌብሩዋሪ 25 ቀን ከ5 - 6 ፒ.ኤም**
ለፌብሩዋሪ 25 ቦታ ይያዙ

### የማመልከቻ ረቂቅ ግምገማ ክፍለ-ጊዜ 2

**ማክሰኞ፣ ማርች 3 ቀን ከ12 – 1 ፒ.ኤም**
ለማርች 3 ቦታ ይያዙ